

# በዚህ ባንዲራ ስም!

ተሰማ ከተማ 06-16-21

በዚህ ባንዲራ ስም፤ የተፈጸመው ግፍ፤
ሲሉኝ ተራግሜ፤፤
በዚህ ባንዲራ ስም፤ እልፎችን በልቷል ሰይፍ፤
ሲሉኝ ተቀይሜ፤፤
አረ ይሄ ባንዲራ፤
ቋት ነው የመከራ፤
ጥፋት ነው የሚጣራ፤
በግፍ ነው የተሰፋ፤
በኪነት ነው የፋፋ፤
ያሉኝን በሙሉ፤
ደርሶ እንደበደሉ፤
አኩርፌያቸው ኖሬ፤
አይ የሞኝ ነገር፤ አይኔ በራ ዛሬ
ዙሪያውን ተጠምዶ፤ሲጨፈጨፍ ዘሬ።
ስታምጥ ብባንን ፤ትግራይ እናት ምድሬ።

በዚህ ባንዲራ ስም፤ በዚህ ባንዲራ ስም

ያልተፈጸመ ወንጀል፤ያልታየ ሃጢያት የለም።